የሰ/መ/ቁ. 49428

ኅዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካቾች**:- 1. ወ/ሮ ከበቡሽ ልሳነርቅ
2. ወ/ሮ መና ገብረ አጋይስት } የቀረበ የለም

**ተጠሪ**:- 1. አቶ ፀዳሉ አዳነ የቀረበ የለም

2. የጐንደር ከተማ አገ/ጽ/ቤት- ከክርክር ውጪ ሆኗል፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የቤት ሽያጭ ውልን አፈፃፀም የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ ነው፡፡ የዳኝነት ጥያቄውም ጥር 9 ቀን 1989 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከ1ኛ አመልካች የገዛውን ቤት ስመ ሐብት እንዲያዛውርለት እና ካርታ በስሙ እንዲሰራለት ማዘጋጃ ቤቱ ተጠይቆ ፈቃደኛ ስላልሆነ በፍርድ ሃይል ተገዶ ይፈጽምልኝ የሚል ነበር፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ ያከራከረው የከተማ ነክ ፍ/ቤት ማዘጋጃ ቤቱ አስተዳደራዊ ተግባሩን እንዲያከናውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የአመልካቾችን መቃወሚያ ባለመቀበል ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሰረት አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለከተማው ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አልተቀበለም፡፡

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕግ ስሕተት የለውም በማለት አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ከመረመረ በኂላ የጐንደር ከተማ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት

ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውንና ተጠሪ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ የሽያጭ ውል በማቅረብ ስም ይዛወርልኝ፤ ካርታ ይሰራልኝ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው ወይንስ የለውም? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በይዘቱ ሲታይ የ1ኛ ተጠሪ ክስ በይርጋ ያልታገደ ስለመሆኑ፣የተጠየቀው ዳኝነትም በሕግ የተመሰረተ ውል መሰረት ያደረገ ስለመሆኑና የጐንደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና በግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘውን ጭብጥ መሰረት አድርገን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ የጐንደር ከተማ ፍ/ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣንን በተመለከተ ነው፡፡ በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በሕግ የሚወሰን መሆኑ እሙን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በግዥ ውል የተላለፈለትን መብት መሰረት በማድረግ የከተማው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥን የሚመለከት ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በአማራ ብ/ክ/መ/በወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ደንብ ቁጥር 12/2000 በተደነገገው መሰረት ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል በማለት ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች የወሰኑት ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን እንደተሰጣቸው በሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሥልጣን መሰረት የለውም የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ውልን በመያዝ ክስ የማቅረብ መብት አለውን? የሚለውን በተመለከተ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው 1ኛ ተጠሪ በግዥና ሽያጭ ውል ያገኘውን መብት መሰረት በማድረግ 2ኛ ተጠሪ ስም የማዛወር ግዴታ እና ካርታ የመስጠት ተግባር አልተወጡም በሚል መነሻ ክስ አቅርቧል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 33945 በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው ገዥ በሽያጭ ውሉ መሰረት ስም ይዛወርልኝ ጥያቄን መሰረት በማድረግ ሻጭ ላይ የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም፡፡ ይልቁንም ይህ ተግባር የአስተዳደር አካል ተግባር ነው በሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን የከሰሰው የአስተዳዳር ተግባር አልተወጣልኝም በሚል ነው፡፡ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሰበር መዝገብ ውሳኔ መረዳት የሚቻለውም አስተዳደሩ በሕግ የተሰጠውን ተግባር ካልተወጣ ገዥ መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚገበው በአስተዳደር አካሉ ላይ ስለመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚቻል ሆኖ አላገኘውም፡፡ በመሆኑም የ1ኛ ተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በሕግ አተገባበር ወይም አፈፃፀም ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ለዚህም ወሳኔው ባለበት ሁኔታ ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በጐንደር ከተማ ነክ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00449 በ01/07/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፣የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00226 የሰጠው ትእዛዝ እና የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 01571 በ29/10/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሳኔ 2ኛ ተጠሪ የሚያቀርቡትን የሽያጭ ውል መነሻ ያደረገ የመብት ጥያቄ የሚገድብ አይደለም፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ